ረቂቅ

# የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት
# The Coalition of Ethiopian Opposition Political Organizations (CEOPO)

*Y.CEOPO Postfach 102409, 60024 Frankfurt – Germany,* *e-Mail* CEOPO@T...online.de *TEL./FAX: +49-69 37108840*

መጋቢት 27 ቀን 1991 /05/04/99

ለክብርት ዶ/ር ጸሃይ ብርሃነ ሥላሴ
የኢሃፓ ተጠባባቂ ሊቀመንበር
በቅድሚያ የአክብሮት ሰላምታችንን እናቀርባለን

የኢተፖድህ አስተባባሪ ኮሚቴ መጋቢት 17 ቀን 1991 ዓ.ም. በአምስተርዳም ከተማ ሶስተኛ መደበኛ ስብሰባውን ባካሄደበት ወቅት ከኢሃፓ ጋር ስለሚኖረው የትብብር ግንኙነትና በተለይም ደግሞ ለህብረታችን አመራርና ለአባል ድርጅቶች በተናጠል በጻፋችሁቸው ደብዳቤዎች ዙሪያ በሰፊው ተወያይቷል::

በአንድ በኩል ለኢተፖድህ አመራር የተላከው ደብዳቤ የኢትዮጵያን ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ለማስተባበር ስለተደረገው ጥረት ከኢሃፓ መሠረት አንስቶ በመጀመሪያው የፓሪስ ጉባኤና የአዲስ አበባ ጉባኤ እንዲሁም በጳጉሜ 1990 ዓ.ም. በቤተሳይዳ በተካሄደው ስብሰባ አልፎ እስከ ሁለተኛው ፓሪስ ጉባኤና የኢተፖድህ ምሥረታ ያለውን የትግል ጉዞ ይዳስሳል:: ከዚያም ባለፈት አወንታ ነጥቦችና ክንውኖች ላይ ለመገንባትና የጋራ ግንባሩን ምሥረታ ሂደት ለማፋጠን ከሚል ተነስቶ "የጋራ ራእያችንን የያዘ ሰነድ ለመንደፍና ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ለመጥራት መንገድ ለመጥረግ" አንድ ስብሰባ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቅሶ ኢተፖድህ በዚህ ስብሰባ ላይ እንዲገኝ ግብዣ ያደርጋል::

በሌላ በኩል ደግሞ ለኢተፖድህ መሥራች አባላት ለሆኑ ድርጅቶች በተናጠል የተጻፈው ደብዳቤ ስለህብረታችን ምንም ሳያነሳ እስካሁን የተከተለው ሁሉ "የተወሰኑ ድርጅቶችን" ብቻ በማቀፍ "በተናጠልና መለስተኛ በሆነ ግንባር ደረጃ" የተከተለ በመሆኑ የተፈለገውን ለውጥ ባለማምጣቱ "ሁሉን አቀፍ የሆነ የጋራ ግንባር መመሥረቱ አማራጭ የሌለው ጉዳይ" ሆኖ መገኘቱን ካረጋገጠ በኋላ የኢተፖድህ አባል ድርጅቶች የኢሃፓ ሴኔት አባል በመሆን የተባለውን "ሁሉን አቀፍ ግንባር" በመመሥረቱ ሂደት እንዲተባበሩ ጥሪ ያደርግላቸዋል::

ካስፈለገ ወደፊት በሰፊው ልንመለስባቸው ብንችልም በሁለቱ ደብዳቤዎች መሃከል ስላሉት ቅራኔዎች ለማተት ለጊዜው ፍላጎቱም ጊዜውም የለንም:: ለህብረታችን አመራር በተጻፈው ደብዳቤ ላይ የተነሱት "ባለፈው ላይ የመገንባት፣ የጋራ ራእይ፣ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ" ጥያቄዎች ለአባል ድርጅቶቻችን በተጻፈት ደብዳቤዎች ላይ አለመኖራቸው፣ ለእነዚህኞቹ በተጻፉት ደብዳቤዎች ላይ የተነሳው የሴኔት አባልነት ግብዣ ለአመራሩ በተላከው ደብዳቤ ላይ መዘለሉ ተቃዋሚዎቻችን እናሰባስባለን ብላችሁ በጀመራችሁት ጉዞ የምትከተሉትን ስትራቴጂ በግልጽ እንዳንገነዘበው አድርጎናል:: ይህም ሆኖ ኢሃፓ ባለፈት ሶስት ዓመታት በዚህ ጉዳይ



አፋር አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር፤ በኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት፤ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ትንቅንቅ፤ የኢትዮጵያ መድህን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ፤ ኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኅብረት፤ ትግራይ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ትብብር፤ ትግራይ-ትግሪኝ ኢትዮጵያውያን ለሶሻል ዲሞክራሲ፤
AFAR DEMOCRATIC REVOLUTION UNITY FRONT;— COUNCEL OF ALTERNATIVE FORCES FOR PEACE & DEMOCRACY IN ETHIOPIA;— COALITION OF ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES;— ETHIOPIAN MDHIN DEMOCRATIC PARTY;— OROMO NATIONAL CONGRESS;— SOUTHERN ETHIOPIAN PEOPLES DEMOCRATIC COALITION;— TIGRAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY;— TIGRAI-TIGRIGNI ETHIOPIANS FOR SOCIAL DEMOCRACY;

ብዙ የደከመና አሁንም በመድከም ላይ የሚገኝ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ለማሰባሰብ የሚደረገው ጥረት የማይነጠል አካል አርገን ስለምንቆጥረው ቅንነት በተሞላው መንፈስ ከናንተ ጋር ለምንፈልገው ውይይት ይረዳ ዘንድ በኢተፖድህ በኩል በዚህ የተቃዋሚ ኃይሎች መሰባሰብ ጉዳይ ያለንን አስተሳሰብ ነጥብ በነጥብ ለማስቀመጥ እንወዳለን::

እስከገባንና ከሁለቱ ደብዳቤያች አውጣጥተን እስከደረስንበት ድረስ የኢሃጉ ጥረት በአንድ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ አማካኝነት አንድ የጋራ ራእያችንን የሚያንጸባርቅ ሰነድ ተነድፍ በዚያ መሠረትነት አንድ ሁሉን አቀፍ የሆነ የጋራ ግንባር መመሥረት ይመስለናል::በና ግምት በኢሃጉ ደብዳቤ ላይ «አወንታዊ ክስተቶች» ተብለው የተፈረጁት የፖሪስ ሁለት ጉባኤና የኢተፖድህ መመሥረት ለነዚህ ተገቢ ጥያቄያቻችሁና ከሃገር ፍቅር የመነጩ ጭንቀቶቻችሁ የመለስ ጥንስስ ይዘዋል እንላለን:: ከዚህም ተነስተን «ባለፉት አወንታዊ ሂደቶችና ክስተቶች» የመገንባት ፍላጉታችሁን ስትገልጹልን በነዚህ ላይ አብረን እንገንባ ብለን ጥሪ እናደርግላችኋለን:: ይህንን የምንለው ኢተፖድህ ያለቀለት ሁሉን አቀፍ ግንባር ነው ከሚል መመጻደቅ ሳይሆን ስለሁሉን አቀፍነት ሂደትም ሆነ ስለጋራ ራእይ ሰነድ ይዘት ከኢሃጉ ለየት ያለ አስተሳሰብ ያለን ስለመሰለን ነው::

1ኛ/ ኢተፖድህ ሁሉን አቀፍ ባይሆንም ሁሉን ሊያቅፍ የሚችል ህብረት ነው::

በዚህ 'ሁሉን አቀፍ' በሚባለው ጉዳይ የኢሃጉ አስተሳሰብ ትንሽ ግራ እንዳጋባን አንሸሸጋችሁም:: እስካሁን የተሰራው ሁሉ «የተወሰኑ ድርጅቶችን ብቻ ያቀፈ» ውሱን ስብስብ ነው ከሚለው በመነሳት አንድ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ አድርጉ አንድ ሁሉን አቀፍ ግንባር የመመሥረት ሃሳብ ይዛችሁ ተነስታችኋል:: እና ግን 'ሁሉን አቀፍ' የሆነ ድርጅት የትም ሆነ መቼም በአንድ ጊዜ ተገንብቶ አያውቅምና ለኢትዮጵያ ዲሞክራቶች ብቻ እንዲህ ዓይነቱ የሩሪ በአንገት አጥልቁ ጥያቄ የሚቀርብበት ምክንያት አይታየንም:: በኢተፖድህ እምነት የአንድ ስብስብ ወይም ግንባር ታጋይነትና ህያውነት የሚለካው ከአመሰራረቱ ሁሉን አቀፍ በመሆኑ ወይም ባለመሆኑ ሳይሆን እያደር ሁሉን ለማቀፍ የሚያስችለውን ሂደት ከጸናነሱ መቀየሱ ወይም አለመቀየሱ ታይቶ ነው:: ይህ ደግሞ ለመዘን የሚችለው ህብረቱን ወይም ግንባሩን የመሰረቱት «የተወሰኑ» ድርጅቶች በሚያጸድቁት የጋራ መታገያ ሰነድ ሁሉን የማቀፍ ችሎታና መሰረታቸውን ለማስፋት፣ ተባባሪያቸን ለማብዛት፣ ደጋፊያቸን ለማፍራት በሚቀይሱት ስትራቴጂና በዚህ ተመርኩዘው ለመራመድ በሚያሳዩት ታታሪነት ብቻ ነው::

«በተወሰኑ ድርጅቶች» የተጀመረ «መለስተኛ ግንባር» ወደዚህ ሁሉን አቀፍነት የሚጓዘው በዚህ ዘዴ ብቻ ነው:: ኢሃጉም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች ይህንን የእድገት ጉዳና ትተው ሁለትም ሰስትም አዳዲስ ድርጅቶችን በተጨማሪ እያካተቱ 'ሁሉን አቀፍ' ግንባር ለመመሥረት ሲፈልጉ አዲስ የጋራ ሰነድ፣ አዲስ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ከተባለ በደብዳቤያችሁ የተመኛችሁት የጋራ ግንባሩን ምስረታ 'ማፋጠን' ጉዳይ የሚሳካ አይመስለንም:: እንዲህ ዓይነቱ የውሃ ቀዳ ውሃ መልስ አካሄድ ለሃገራችንና ለህዝባችን ካለን የተቀደሰ ዓላማ አንጻር ሲታይ እዚህ ግባ የማይባለውንንና እጅ ተወርች አስሮ የያዘንን የገንዘብ አቅም ማባከን፣ ትኩረትን መበተን፣ ሂደትን ማዝረክረክና የመጨረሻ መጨረሻም የሃገራችንን ዲሞክራቶች የጋራ ትግል ጉዳይ ከርሞ ጥጃ እንዳያደርግብን እንሰጋለን::ከዚህ ይልቅ የምንመርጠው ኢሃጉ «እስካሁን በተሠራው ላይ መገንባት» ባለው አቋሙ ላይ ጸንቶ ቢቆምና በፖሪሱ ጥንስስ ላይ በጋራ ስለምንገነባበት ሂደት ከኢተፖድህ አመራር ጋር ትርጉም ያለው ውይይት ለማካሄድ የሚያስችል ሁኔታ[illegible]መቻቸት እንደሆነ ልንገልጽላችሁ እንወዳለን::

2ኛ/ የኢተፖድህ ሰነድ ሁሉን ሊያቅፍ የሚችል ሰነድ ነው::

'የዲሞክራሲ ሂደትና የነጻ ምርጫ ትግል' የተሰኘው የኢተፖድህ ሰነድ የብዙ ውይይት፣ ውጣ ውረድና የትግል ልምድ ውጤት እንደመሆኑ መጠን በሃገራችን የሚገኙ ዲሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ኃይሎችን በሙሉ ለማሰባሰብ በሚያስችል መልክ የተነደፈ ሰነድ ነው:: የዚህን ሰነድ ሁሉን አቀፍነት ለማረጋገጥ የተከተልነው ዘዴ ቀላልና ግልጽ ነው:: በሃገራችን አሉ የሚባሉም ሆነ ወደፊት ሊፈጠሩ የሚችሉ ድርጅቶች ዲሞክራቲክና አገር ወዳድ ነን እስካሉ ድረስ በየፕሮግራማቸው የያዟቸውን ወይም ሊይዟቸው የሚገባቸውን የጋራ ነጥቦች በሙሉ እና እነዚህን የጋራ ነጥቦች ብቻ በማሰፈር የተቀመጠ ሰነድ ነው:: እነዚህ ከሁሉም ድርጅቶች ፕሮግራሞች የተለቀሙት የጋራ ነጥቦች ዲሞክራሲን፣ ሰብአዊ መብትን፣ የሕግ የበላይነትን፣ የሕዝቦች እኩልነትን፣ የሃገር ሉዓላዊነትና አንድነትን፣ ነጻ ምርጫና ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥትን የሚመለከቱ ሕጎች ተቀነባብረው በፖሪሱ ሰነዳችን ውሉን በመጣስ የጋራ ትግላችን መመሪያ ለመሆን በቅተዋል::

ወደ ሁሉን አቀፍነት የሚንጠራራ ማንኛውም ሰነድ የፖሪሱ ሰነዳችን ከያዟቸው ነጥቦች ቀንሶና ዝቅ ብሎ ከተገኘ ተቃዋሚ ኃይሎች በምን መድረክና ለምን ዓላማ በጋራ ለመታገል እንደሚችሉ ለማየት ያስቸግራል:: ኢሃን እንዳቀረበው ሰነድ ደግሞ ከዚህ ከፍ ብሎ በአንዳንድ ድርጅቶች ፕሮግራሞች ላይ ያሉ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፖሊሲ ምርጫዎች እያንጸባረቀ በሌሎች ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች በእነዚሁ ጉዳዮች ላይ የሰፈሩትን ምርጫዎች ወደ ጎን ከተወ ደግሞ ወዲያውኑ ወገናዊነቱ ይንጸባረቅና የሁሉን አቀፍነቱ ነገር ያከትምለታል ማለት ነው::

ይህ ስለተባለ ስምንት ድርጅቶች ያጸደቁት ሰነድ በሂደት ውስጥ ከህብረቱ ሊደባለቁ በሚሹ ኃይሎች የመሻሻልና የመዳበሩ እድል የተቀላለፈ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: የፖሪሱን ጉባኤ ለማሰናዳት በሰኔ ወር 1990 ዓ.ም. በአምስተርዳም በተደረገው ስብሰባ ላይ ከፖሪሱ ጉባኤ በኋላ ከሚፈጠረው ህብረት ለመደባለቅ ለሚፈልጉ ድርጅቶች ሰነዱ ተቀላልፎ እንዳይጠብቃቸው ጥንቃቄ በመወሰዱ እነዚህ ድርጅቶች ሰነዱን ለማሻሻልና ለማዳበር 'ገንቢ አስተዋጽኦ' የማድረግ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን አረጋግጧል::

3ኛ/ በኢተፖድህ ዙሪያ ዲሞክራቶችንና አገር ወዳዶችን ለማሰባሰብ ስለተቀየሰው ስትራቴጂ

በዚህ የጋራ ሰነድ ዙሪያ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው ስለሚታገሉበት ሁኔታ ኢተፖድህ በሶስት የተቀነባበሩና የሚተጋገዙ አቅጣጫዎች ስትራቴጂውን ቀይሶ በመሥራት ላይ ይገኛል:: ይህ ስትራቴጂም ጥር 22 ቀን 1991 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ለተደረገው ህዝባዊ ስብሰባ በሰፊው የተብራራ ሲሆን እንደሚከተለው ሰፍሯል፣

ሀ/ ሌሎች ዲሞክራሲያዊና አገር ወዳድ የፖለቲካ ድርጅቶች ከኢተፖድህ እንዲደባለቁ ጥሪ ባደረግንበት የመልእክታችን ክፍል

«የኢተፖድህ የትግል መድረክ ወገናዊ የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም አይደለም:: የማንንም አባል ድርጅት የግል ዓላማ፣ የፖለቲካና የርእዮተ ዓለም ምርጫ ለማራመድ የተመሠረተ ህብረት አይደለም:: ከዚህ ይልቅ በዘመናት የግፈኞች አገዛዝ ደርበው የተላጠው የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ ድምጹ የሚሰማበትና ከቁጥር የሚገባበት፣ በህግ የበላይነት የሚተዳደር ህብረተሰብ ለመፍጠር ነው:: በዚህ ትግል ዲሞክራሲ ሰፍኖ ለነጻና ርትአዊ ምርጫ ሁኔታዎች ሲመቻቹ የኢተፖድህ ተልእኮ ይጠናቀቃል:: አባል ድርጅቶችም ሆኑ

ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የየራሳቸውን ፕሮግራም ይዘው በትግላችንና በትግሉ የገዛ እድሉ ባለቤትና በሉዓላዊት አገሩ ሉዓላዊ በሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ፊት ለውድድር ይቀርባሉ:: በመሆኑም በዚች በሃገራችን ያሉ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ ለዚህ ዓላማ ከኢተፖድህ ጋር የማይተጋገዙበት ምንም ምክንያት ስለማይታየን ከትግሉ እንዲደባለቁ ጥሪ እናደርግላቸዋለን::" በማለት ለፖለቲካ ድርጅቶች መልእክቱን አስተላልፏል::

ለ/ ከፖለቲካ ውጭ ያሉ የሙያ ማህበራትም ሆኑ ሌሎች ስብስቦች ጋር ስለመተጋገዝ ጉዳይ በሚያነሳው የመልእክቱ ክፍል፣

"የኢተፖድህ ትግል ህብረተሰባችንን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ የሚደረግ ትግል ስለሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች ትግል ብቻ ሊሆን አይችልም:: ዴሞክራሲ ደብዛው ጠፍቶ የዘፈቀደ አገዛዝ እስከሰፈነ ድረስ ሠርቶ አደሩ ከድካሙ ፍሬ ተገቢ ድርሻውን ለማግኘት፣ ነጋዴውም ሆነ ባለ ኢንዱስትሪው ጥሮ ግሮ ተገቢ ጥቅሙን ለማዳበር፣ ጋዜጠኛው ሆነ መምህሩ፣ ምሁሩ ሆነ የመንግሥት ሠራተኛው ሙያቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበር በአጠቃላይ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በነጻ ተደራጅተው ለጥቅማቸው፣ ለመብታቸውና ለህልውናቸው የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም:: በመሆኑም የኢተፖድህ የዴሞክራሲ ትግል እነዚህን ኃይሎች ሁሉ የሚመለከት በመሆኑ ከዚህ ትግል እንዲደባለቁና ለዚህ ቅዱስ ዓላማ እንድንተጋገዝ ጥሪ እናደርግላቸዋለን" ብሏል::

ሐ/ ዴሞክራትና አገር ወዳድ ግለሰቦች ሁሉ በያሉበት ኢተፖድህን እንዲደግፉ በሚጠራው የመልእክቱ ክፍል፣

«የኢተፖድህ ትግል ከፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ ከሌሎች ስብስቦች ትግል አልፎ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ዜጎቻችንም የሚመለከት የመብትና የዴሞክራሲ ትግል ነው:: በዘፈቀደ አገዛዝ ስር እስካለን ድረስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በዚህ አገዛዝ ግፍ የማይጉነጥ፣ ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ ሊጎናጸፍ የሚገባውን ክብርና መብት የማይገፈፍ፣ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ መላበስ የሚገባውን የዜግነት ጸጋና መብት የማይነጠቅ ግለሰብ አይኖርም:: በመሆኑም ትግሉ የመብትና የዴሞክራሲ ትግል በመሆኑ በሚልዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንም እንደራሳቸው ዓላማ አርገው ሊዋደቀለት ይገባል

"የኢተፖድህ ትግል የሃገር ፍቅርና የሃገር ክብርም ትግል ነው:: በሰፈነው ጸረ ዴሞክራቲክ አገዛዝ የተነሳ ኢትዮጵያችን ነጋ ጠባ በሰብአዊ መብት ተሟጋች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስትወገዝና በስመ ጥፉነት ስትነሳ የሚሸማቀቀው፣ ይቺን አገር ከአኩሪ ታሪኳና ባህሏ፣ ይህ ነው ከማይባል የተፈጥሮና ሰብዓዊ ሃብቷ ተመጣጣኝ የሆነ ልማትና ብልጽግና የማጎናጸፍና በዓለም ህዝቦች ሸንጎ ተገቢ ቦታዋን የማስያዝ ራእይ ያለው አገር ወዳድ ሁሉ ይህ ራእይ የኢተፖድህም ራእይ፣ ትግሉ የኢተፖድህም ትግል መሆኑን ተገንዝቦ በሚፈቅደው፣ በሚችለውና በፈለገው አቅምና መስክ ይህንን የተቀደሰ ዓላማ በማገዝ እንዲተባበረን ጥሪ እናደርጋለን» ብሏል::

የኢተፖድህ አመራር 'ባለው ላይ የመገንባት' ሂደት ከፍ ብለን በዘረዘርናቸው አግጣጫዎች የሚገለጽ ሲሆን እስካሁን ድረስ በዚህ መልክ ትግሉን ለማጠናከር የፖለቲካ ድርጅቶች ከኢተፖድህ በአባልነት እንዲደባለቁ፣ የሲቪክ ማህበረሰቡ ስብስቦች እንዲተባበሩን እንደዚሁም ኢትዮጵያውያን በድጋፍ ኮሚቴዎች መልክ እየተደራጁ እንዲደግፉን አስፈላጊ የሆኑትን ርምጃዎች እያጠናን በተግባር በመተርጎምና የጋራ ትግላችንን መልክ በማስያዝ ላይ እንገኛለን::

4ኛ/ ኢሃግና ኢተፖድህ ስለሚኖራቸው ግንኙነት

ከፍ ብለን ከዘረዘርነውና ከምንቀጥልበት የትግል ስትራቴጂ አንጻር ሲታይ ከኢሃግ ጋር ያሉት ችግሮች ግልጽ ናቸው:: እንደማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት በስምንቱ ድርጅቶች ላይ ዘመነና አባል ሆናችሁ ተደባለቀን እንዳንል ኢሃግ የፖለቲካ ድርጅት አይደለም:: ለሲቪክ ስብስቦች ባለን ስትራቴጂ መሠረት እንተባበር እንዳንል የፖለቲካ ግንባር ለመመሥረት የሚጥር ኃይል ነው:: እንደ ዲሞክራትና አገር ወዳድ ግለሰቦች በድጋፍ ኮሚቴ አማካኝነት ደግፈን እንዳንለው ስብስብ ነው::

ተደጋግሞ የተባለውና ለኢተፖድህ አባል ድርጅቶችም በተላከው ደብዳቤ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው "የኢሃግ ዋና ዓላማ ሁሉን አቀፍ የሆነ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ ግንባር እንዲፈጠር ማድረግ ሲሆን ህብረቱ ከተፈጠረ በኋላ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘው መንገድ ሁሉ መርዳት ነው::" ተብሏል:: ፓሪስ የተፈጠረው ህብረታችን ለዚህ ሁሉን አቀፍ የሚሆን ግንባር መሰረት ከመጣሉም በላይ ከዚያ ወዲህ የተከተልነው የትግል ስልት የዚህን ህብረት እድገት እያጠናከረ የሚሄድ ስልት ነው::

በኢተፖድህ እምነት ሁለቱ ሂደቶች መተጋገዝ እንጂ መጠላለፍ የለባቸውም:: ይህንን ሁኔታም በማጤን ህብረታችን ተመስርቶ ወር ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ለኢሃግ አመራር ስለወደፊቱ ትብብራችን እንወያይ ዘንድ አንድ ደብዳቤ መጻፉ ይታወሳል:: ለዚህ ደብዳቤያችንም የተሰጠው መልስ በጉዳዩ ውይይት በመካሄድ ላይ እንደሆነና አመራሩ በዚህ ጉዳይ ያለውን አስተሳሰብ ወደፊት እንደሚገልጽ የሚያበስር መልስ ነበር:: ይህንን አስተሳሰባችሁን ለማወቅ ጊጋትን በመጠበቅ ላይ እንዳለን ከላይ የጠቀስናቸው ሁለት ዓይነት ደብዳቤዎች ለህብረታችን አመራርና ለአባል ድርጅቶቻችን ደረሱ:: እነዚህ የሁሉን አቀፍ ጉባኤና የሁሉን አቀፍ ግንባር ምስረታ ጥሪዎች ኢተፖድህና ኢሃግ በጋራ ስለሚሰሩበት ሁኔታ እንድንወያይ ላቀረብነው ጥያቄ በቂ መልሶች አይደሉም::

ከዚህ ይልቅ አሁንም ደግመን የምናቀርበው ጥያቄ እንወያይ የሚል ነው:: ለዚህም ውይይት እንዲያግዝ በማሰብ የኛን ሂደት ለማብራራት ይህንን ረጅም ደብዳቤ ልከናል::ይህ ሂደታችን ኢሃግ ከሚከተለው ተቃዋሚያችን የማሰባሰብ ስትራቴጂ የት ላይ እንደሚስማማ፣ የት ላይ እንደሚጋጭ፣ የት ላይ እንደሚጣጣምና የት ላይ እንደሚጠፋፋ በጥሞና መርምራችሁ ከዚህ ሁሉ አንድ የጋራ አይታ እንዲገኝ ያላችሁን አስተሳሰብ ገለጹልን::

የእንዲህ ዓይነቱ ውይይት መካሄድ ለትግላችን አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለን ስለምንገምት ለዚህ ቅድሚያ በመስጠት እስከዚያው ድረስ ኢተፖድህም ሆነ አባል ድርጅቶቹ በነዚህ ትግላችንን ያገዙ ወይስ ያደናቀፉ በውል ባልተበራፉ ሁሉን አቀፍ ጉባኤና ሁሉን አቀፍ ግንባር ምስረታ ሂደቶች ከመሳተፍ እንዲቆጠቡ በኢተፖድህ አስተባባሪ ኮሚቴ ስስተኛ መደበኛ ው ስብሰባ ላይ በሙሉ ድምጽ የተወሰነ መሆኑን እየገለጽን ከሰባት ወር በፊት አንስተን አሁንም ከምንደግመው የውይይት ጥሪ አወንታዊ መልሳችሁን በመጠባበቅ ላይ መሆናችንን በትህትና እንገልጻለን::

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

የኢተፖድህ [illegible] ኮሚቴ
ሴክሬታሪያት

4ና/ ኢሃጕና ኢተፖድህ ስለሚኖራቸው ግንኙነት

ከፍ ብለን የዘረዘርነው የኢተፖድህ ሂደት ኢሃጉ ከቀየሰው የግ